# ወዮላቹህ!

EthioLion የጐንቻው !

ወዮላቹህ፤የቀን ጅቦች ሳታስቡት፤መሸባቹህ፤
ሕዝብ መሸጓል በዋሻቹህ፤መሸሸጊያም የላቹህ፤
አጥንት ነካሽ ‘የቁራ ውሾች’፤ተራብታቹህ፤
ስትጮሁ ለከርሳቹህ፤የሕዝብ እሮሮ ነቅፋቹህ፤
ምንደኞቹ፤ሕዝብ-አገር በቅርጫ ያረዳቹህ፤
ምረነኛ፤ጉጅሌዎች ‘ስጋ-በስጋ’ የደለባቹህ፤
እርም እምነት የበላቹህ፤በዘር በደም ተሳከራቹህ፤
የወየናቹህ፤በእብሪት በጥጋብ ተወጥራቹህ፤
ጎኑ ቀዷል፤ሊያባራ ነው ምጣችን፤ምጣታቹህ፤
በዓለም መስትዋት የበቀል ቁና ፍዳቹህ፤
ተቆልሏል፤አበሳቹህ፤ልክ ያለፈ ስንክሳራቹህ፤
እንዳይነቱ ግብራቹሁ፤የአደባባይ ፍጻሜያቹህ፤
**እንደ ቱኒዙ፤ግብጽ፤ሊብያ፤ ነው እጣ ፋንታቹህ።**

በቁስላችን እሾህ የምትሰዱ፤የወያኔ፤ቁንጮዎች፤
እሾሁ ሲነጣጠር ወደ አይናቹህ በሚሊዎኖች፤
በሞተ ሰዓት የሟርት ሽብር ከበሮ ደላቂዎች፤
ስንቱን ክቡር ዜጋ ጭቃ ቀቢ፤የአገር ጉድፎች፤
የምታስሩ፤የምትገርፉ፤ወንድም፤ እህት፤ወላጆች፤
‘ቴሬሪስት፤ድራጊስት፤አልካኢዳ፤አልሸባብ’ ክሶች፤
የወንበዴ ታርጋ ለጣፊዎች፤ምህረት የማትሹ፤ቂሎች፤
‘ዝና-ስሙ’ ለናንተ እንጂ እድራችሁ አጥፍቶ-አጥፊዎች፤
በፓርላማ፤በ‘አረንጓዴው አደባባይ’፤ባዶ ድንፋታዎች፤
አይሰሩምና የ‘ጋዳፊ’ መፈክሮች፤የቅጥፈት ስልቶች፤
**ወዮላቹህ! ፍጻሜያቹህ፤ለምህረትም-ለተረትም አይመች።**

በግንባራችን የደቀናቹህ የወያኔ ‘ጠብ-አንጋቾች’፤
ቃታ ከሳበ ጣታቹህ ዛሬም ልትገድሉ የሕዝብ ልጆች፤
ቅጽፈት ናቹህ፤የሰማይ የምድር ዘላለም ሙቶች፤
በህግና በፍትህ ስም የምትቀልዱ ዳኛ ጠበቆች፤
የምታንገላቷቸው፤የትውልድ የሰላም አንኳሮች፤
የአገር-ሕዝብ አውራ፤ንግሥት ናቸውና እስረኞች፤
**ዛሬ አስተውሉ፤እንዳይነድፏቹህ ኋላ ‘ሆ!ብለው ንቦች።**

የኔሰው ገብሬ፤ የዳውሮ ዋርካው፤ ምሁሩ ሻማ፤በራሱ ለቆ፤
የጋረደንን የፍርሃት ድባብ በኃይዎቱ፤ውጋገን ለኛ፤ፈንጥቆ፤
አይሆንምና ደመ-ከልብ ቃል በምድር፤ቃል በሰማይ፤ተሰንቆ፤
**እንዲጧጧፍ ትግላችን በየጉልቻው፤አናዳጆችን ማግዶ፤አስጨንቆ።**

ወዮላቹህ! ወያኔዎች፤‘ሙባረክን’፤‘ጋዳፊን’ ያዩ፤
እዝነ-ልቦናቹህ፤ክልፈራ፤ዓይነ-ህሊናቹህ፤ካላዩ፤
እንደ ደመራ ልትሞቁን ከዳዳቹህ፤ሕዝብ ሲቃጠል እየታዩ፤
ኢትዮጵያዊ በግፋቹሁ እየጋዩ፤ንስሃቹህ፤ከዘገዩ፤
**ወዮላቹህ፤ወገን ጥዶ ያብስላቹህ መስቀል ከበ እያጋዩ።**

Ethiopia Will Prevail!

EthioLion.Com

እነሆ፤የተዳፈነው እሳት፤ተቀጣጥሏል፤ሰደዱ፤
የተቆጡት፤የቆረጡት፤በየማዕዘኑ፤ሊነጉዱ፤
‘የፎጡን’፤ግንብ፤ሊንዱ፤ቅልቦችን ሊያስርዱ፤
ወዩላቹህ!፤ሕዝብ ሃያል ነውና የቁጣ ክንዱ፤
መውረጃቹህ ይኸኔ ነው፤ብትሰሙ፤ብትረዱ፤
በግብጽ ‘ሙባረክ’፤ሕዝብ የናቁት፤ ‘አንበሳ’፤
እንደ ጨርቅ አልቀው ሲጓጓዙ በሳንሳ፤
አልጋ ወራሾች፤ተሳስረው ከንጉሱ፤ቁም እሬሳ፤
የሊቢያው ‘ጋዳፊ’፤ሕዝብን በስድብ አርክሰው፤
ተጐተቱ፤ከአይጥ ጉድጉድ ተወትፈው፤
ተዋርደው ሞቱ፤ያልማሩትን ሕዝብ ምህረት ለምነው፤
ወዮላቹህ! ወያኔዎች፤በደመ ነፍስ፤ያላቹህ፤
ቅንጣት እምነት ካላቹህ፤በደል ጥፋታቹሁን፤አምናቹህ፤
**ንስሃ ግቡ፤ባለቀ ሰዓት ሽብር አሳሩን ትታቹሁ።**



## ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት መስዋዕቱ፤ ሰማዕታቱ የኔሰው ገብሬ! ዳውሮ-ዋርካ

*በወያኔ በደልና ግፍ ተንገብግቦ ሕይዎቱን በአደባባይ ለወገኑና ለሐገሩ መስዋዕትነት በቁሙ እሳት ኢጋይቶ የመጨርሻውን የሕይዎት ዋጋ ለከፈለው ጀግናው ወጣት ምሁር የኔሰው ገብሬ መታሰቢያ ትሁንልኝ።*

*እነሆ አምላካችን ነፍሱን ይማርልን፤ ለወላጅ ቤተሰቦችም ጽናትን ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ቆራጥነትን፤ እሻለሁ፡ ወንድማችን ደመ-ከልብ ሆና እንዳይቀር መልዕክቱን፤ተቀብለን መስዋዕትነቱን ግብ እናድርስ፡ የትግሉን ሰደድ አቀጣጥለን፤ለድል እንብቃ፤የሰማዕታቶቻችንን ነፍስ ይማር።*

*የወጣቱ ምሁር የኔሰው ገብሬ እንደ ቱኒዚያው መሐመድ ቡዋዚዚ ለዓረብ ሕዝብ ተምሳሌ ሆኖ በርካታ ህሕዝቦንችንና አገራትን ከዘመናት ከባርነት ያልተለየ አገዛዝ ነፃነት እንዳቀዳጀና እያቀዳጀም እንዳለው ሁሉ፤ የቆራጡ ወንድማችን ገድልም ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን እንደኛ በጨካኝ፤ገዥዎቻቸው ስር ለሚማቅቁ፤ ጥቁር አፍሪቃዊያን ወገኖቻችን ሁሉ፤የነጻነት ቀንዲል ይሆናል።*

**የጐንቻው!** yegonchaw@yahoo.co.uk